# የአማራ ሀገር አቀፍ የፖለቲካ ድርጅት የመመሥረት አስፈላጊነትና ዓላማ አደረጃጀቱ!

ጃንቶሐራ!

ከዚህ ቀደም የምታውቁኝ በቀንደኛ የዘውግ ፖለቲካ ተቃዋሚነቴ ነበረ፡፡ በአማራ ስም የፖለቲካ ጅርጅት ለማቋቋም በዕውቀት ሳይሆን በእልህና በስሜት ተነሳሥተው ሐሳብና ሙከራ ላይ የነበሩ ወገኖችን "አይ! በፍጹም አይሆንም! አይደረግም! ይሄ ለወያኔ ድል ነው! ወያኔ የሚፈልገውስ ምን ሆነና? አማራን ማስፎረሽ አይደለም ወይ? አማራ ጠቦ የሚያውቅበት ዘመን የለም! ሲጀመር ጀምሮ አስተሳሰቡ ሁሉ ሀገርአቀፍ እንጅ ጎጥ ሆኖ አያውቅም፡፡

ይሄንን የእናት አባቶቻችን እሴት ቅርስ ጠብቆ የመቆየት አደራና የሞራል (የቅስም) ግዴታ አለብን! በወቅቱ በነበረው አስገዳጅ ሁኔታ መአሕድ የሚባል ድርጅት ተቋቁሞ የነበረ ቢሆንም የዓላማው ማዕከል ጎጥን ሳይሆን ኢትዮጵያን ያደረገ ስለነበር እስከአሁን የሌለው የዘውግ ድርጅት የአማራ ነውና በአማራ ስም በተለይም ማንነታቸው እንዳልታወቁት ምናልባትም ወያኔ እንደሆኑ እንደሚጠረጠሩት በማኅበራዊ የብዙኃን መገናኛ "ጎጥን ትኩረቱ ያደረገ ተገንጣይ ዘውገኛ የአማራ የፖለቲካ ድርጅት እናቋቁማለን!" እንደሚሉት እንዲህ ዓይነት ድርጅት በአማሮች የተቋቋመ ዕለት ይህች ሀገር ባለቤት ታጣና ያልቅላታል! በማለት እንዲገቱ ያደረኳቸው በርካቶች ናቸው፡፡ "…ነበረ የምታውቁኝ!" ስላቹህ ከዚህ በኋላ ግን ሳወግዘው ስቃወመው ስንቀው የኖርኩትን እጅግ ኋላቀርና ያልሠለጠነ የሆነውን የዘውግ ፖለቲካን አቀነቅናለው ማለቴ መስሏቹህ ከሆነ ተሳስታቹሀል፡፡ በፍጹም ሊሆንም አይችልም፡፡

የዚህ ሊመሠረት ይገባል አስፈላጊ ነው የምለው የአማራ የፖለቲካ ድርጅት ዋነኛ ዓላማም የኢትዮጵያን ሕዝብ በማስተማርና በማሠልጠን ደናቁርቱ ወያኔና ሌሎች የጥፋት ኃይሎች የተከሉበትን ይሄንን እጅግ ኋላ ቀርና ጎጂ ከመሆኑ የተነሣ በሠለጠነው የምዕራቡ የዓለማችን ክፍል ፈጽሞ የማይሠራበትን የተናቀውን የተጠላውንና የተወገዘውን የዘውግ ፖለቲካን ከሀገናችን አጥፍቶ ፖለቲካችን ዜጎችን በሰውነታቸው ብቻ በእኩል ዓይን በመመልከት ፖለቲካዊ እንቅስቃሴው ከጎሳ ተኮር ወይም ዘውግ ውጪ በሆኑ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ሰብአዊ መብቶች ላይ ብቻ አትኩሮ እንዲዘወርና ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት በእነዚህ ነጥቦች ዙሪያ በሚያቀርበው አማራጭና የአስተሳሰብ ልዩነት ብቻ እንዲለካ እንዲዳኝ ማለትም ተመራጭ ወይም ተጣይ እንዲሆን ማድረግ የሚቻልበትን የጸና ምኅዳር ለመፍጠር በዚህም የሀገራችንን ፖለቲካ የሠለጠኑት ምዕራባውያን ከደረሱበት ደረጃ ላይ እንዲስተካከል በማድረግ የአጠቃላይ ሕዝቡ ማለትም የግለሰብን መብትና ከጎሳ ተኮር ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ውጭ የሆኑ የቡድን መብት የተጠበቁባት ፍጹም ዲሞክራሲያዊት (መስፍነ ሕዝባዊት) ኢትዮጵያን መፍጠር ነው፡፡

ከምንም ነገር በፊት ይህ ሥራ ሊሠራ ካልቻለ በስተቀር ዘውገኝነት ካለው ጊዜአዊ አታላይ ባሕርይው የተነሣ ጠባብ ርዕዮተዓለሙ የሚናኝበት ነጻ ምኅዳርና መብት እያለ ሥልጡኑ ሀገር አቀፍና የአንድነት አስተሳሰብ ሊያብብ ሊጎለብት የሚችልበት ዕድል ዝግ በመሆኑ ይህችን ሀገርና ሕዝቧን መታደግ የሚቻልበት

ዕድል አይኖርም፡፡

ይሄንን ስል "የሕዝቡ ሁለንተናዊ አመለካከት ባላደገበትና ባልሠለጠነበት ሁኔታ ፖለቲካዊ አመለካከቱን ነጥሎ ሕዝቡን እንደሠለጠኑት ምዕራባውያን አስብ! ማለት ይቻላል ወይ?" መባሉ የሚቀር አይመስለኝምና ከወዲሁ መልስ ሰጥቸበት ባልፍ መልካም ይመስለኛል፡፡

እጅግ የሚገርማቹህ ጉዳይ ቢኖር የዛሬን አያድርገውና ከዚህ የፖለቲካ ብስለት ደረጃ በመድረስ የሚቀድመን ወይም የሚደርስብን አንድም ሀገር የነበረ አለመኖሩ ነው፡፡ በእነኝህ ዛሬ ሠለጠኑ በምንላቸው የምዕራብና የእስያ ሀገራት ውስጥ በታሪካቸው የብሔረሰብ ወይም የጎሳ ስም ተጠቅሶ በቂና አሳማኝ ባልሆነ ምክንያት የተለየ ጎሳነቱና ገዥነትን በብቸኝነት የታደለ መሆኑ ሲገለጽ በሀገራችን ግን እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ ለአንድም ጊዜ ቢሆን አገልግሎ አያውቅም፡፡

የምላቹህ ገብቷቹሀል? ይሄኔ ያልኩትን ባለመረዳት "አቤት ውሸት! አቤት ክህደት!" በማለት እራሱን ይዞ የሚጮህ በርካታ ሰው ይኖራል፡፡ ልብ ብላቹህ አድምጡኝ! እደግመዋለሁ "በእነኝህ ሠለጠኑ በምንላቸው የምዕራብና የእስያ ሀገራት በታሪካቸው የብሔረሰብ ወይም የጎሳ ስም ተጠቅሶ በቂና አሳማኝ ባልሆነ ምክንያት የተለየ ብሔረሰብነቱ ወይም ጎሳነቱና ገዥነትን በብቸኝነት የታደለ መሆኑ ተገልጾ በዚያ መልኩ ሲገዙ የኖሩ ሲሆን በሀገራችን ግን ለአንድም ጊዜ እንኳ ቢሆን ጎሳ ወይም ብሔረሰብ ለፖለቲካ ፍጆታ ውሎ አገልግሎ አያውቅም!"

እስኪ ማን ነው "እከሌ የተባለ ዐፄ ዘሩ አማራ ነው!" ተብሎ ክብረ ነገሥት ወይም ዜና መዋዕል ላይ ተጽፏል ብሎ የአንድ ንጉሥ ስም ሊጠቅስልኝ የሚችለው? የዐፄዎቻችንን ዘር ወይም ብሔረሰብ በትውፊታዊ መረጃ ካልሆነ በስተቀር ከመዛግብቶቻችን ላይ ተጠቅሶ የሚያውቅ አንድም ንጉሥ ወይም ንግሥት ኖራ ወይም ኖሮ አያውቅም!

እንዳልኳቹህ በትውፊታዊ መረጃ ግን እስከ ንግሥት ማክዳ ወይም ንግሥተ ሳባ ድረስ የነበረው፣ ንግሥት ማክዳ ቀዳማዊ ምኒልክን ከዳዊት ልጅ ከንጉሥ ሰሎሞን በመውለዷ ምክንያት እግዚአብሔር ንግሥናን ከዳዊት ዘር እንደማያጠፋ የሰጠው ቃል ኪዳን ስለነበር በሀገራችንም በመሀል በዛጉዌዎች ለ 333 ዓመታት ያህል ቢቋረጥምና እንደገና ተመልሶ ከይኩኖ አምላክ ጀምሮ እንዲቀጥል ተደርጎ ንግሥና ከዳዊት ልጅ ከሰሎሞን ከተወለደው ከቀዳማዊ ምኒልክ ዘር ወይም ቤተሰብ እንዳይወጣ በማድረግ እስከ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ ድረስ ሀገሪቱን የገዙ ነገሥታትና ንግሥታት ከአማራ ነገድ ወይም ብሔረሰብ እንደነበሩ የሚታወቅ ጉዳይ ነው፡፡

በሰነድ ደረጃ ግን "ዐፄ እከሌ በአባቱ በኩል ከእገሌ በእናቱ በኩል ከእገሊት እንትን ከተባለው ስፍራ ይወለዳል" ከሚለው መረጃ በስተቀር ነገዱ ወይም ብሔረሰቡ ካለመጠቀሱ የተነሣ ለታሪክ ተመራማሪዎች አጥኚዎችና ባለሞያዎች ሳይቀር ነገሥታቱና ንግሥታቱ ከየትኛው ነገድ ወይም ብሔረሰብ እንደተወለዱ ማወቅ አስቸጋሪ ወይም የማይቻል የሆነበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡

የዚህ ምክንያት ደግሞ ምንም እንኳ በትረ መንግሥቱ በአጋጣሚ በጥቅሉ ከሁለት ነገድ ማለትም ከአማራና ከአገው የወጣ ባይሆንም አንዳንዴም ከእነኝህ የነገሥታት ዘር ወይም ቤተሰብ ጋር የመዋለድ ዕድል ያጋጠማቸው ኦሮሞዎች የመግዛት ዕድል ያገኙ ቢሆንም እናት አባቶቻችን እንደ የምዕራቡና የእስያ ሀገራት ተጨባጭና አሳማኝ ባልሆነ የፈጠራ ምክንያት ሌሎች ብሔረሰቦችን ዘራቸው ወይም ብሔረሰባቸው ይሄ ወይም ያ በመሆኑ ምክንያት ብቻ በማግለል በማንኳሰስ የራሳቸውን ነገድ ወይም ብሔረሰብ የተለየና የመንግሥት ሥልጣንን በብቸኝነት የታደለ አድርጎ ማቅረብ ወይም በዘመናዊ አገላለጽ ፖለቲካን በዘውግ ላይ መመሥረት ማለትም በጎሳ ላይ የተመሠረተ ማድረግ የተሳሳተ ያልበሰለና ፍጹም የማይገባ መሆኑን ስለተረዱና ስላመኑበትም ነው፡፡

አሁንም ግር የሚለው ሰው ሊኖር እንደሚችል እገምታለሁ፡፡ ባጭሩ እያወራሁ ያለሁት ስለ ነገድ

ወይም ብሔረሰብ ነው እንጅ በሀገራችን እንደ እስራኤል ሁሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነ ምክንያት የመንግሥት ሥልጣን ከዳዊት ልጅ ከንጉሥ ሰሎሞን ከተወለደው ከቀዳማዊ ምኒልክ ቤተሰብ ወይም ልጆች እንዳይወጣ ተደርጎ ሥዩመ እግዚአብሔር (በእግዚአብሔር የተሾመ) እየተባሉ ሲገዙ ስለኖሩት የአንድ ቤተሰብ ልጆች ጉዳይ አይደለም እያወራሁ ያለሁለት፡፡ ግልጽ ነው?

በመሆኑም ፖለቲካን (እምነተ አሥተዳደርን) በጎሳ ላይ የተመሠረተ ማድረግ ያልበሰለ ያልሠለጠነ ኢፍትሐዊና እጅግ ኋላ ቀር አሠራር የመሆኑ ጉዳይ እኛ ያወቅነውና የደረስንበት እንደሌሎቹ አሁን በቅርቡ በ 19 ኛው መቶ ክ/ዘ ሳይሆን ታሪካችን ሲጀመር ጀምሮ ነው፡፡ በዚህም ልንኮራ ይገባል፡፡

"ታዲያ ምነው አንተው እራስህ "የአማራ" ብለህ የነበረንን በሳል አስተሳሰብ ተቃረንክብን? ከላይ ያልከውን እያልክ ስትነቅፍ ስታወግዝ ስትዘልፋቸው እንደኖርካቸው የወያኔና የጠላቶቻችን ቅፍቅፍ ግለሰቦችንና ቡድኖችን ሆንክ ማለት አይደለም ወይ?" የሚል ጥያቄ ሊነሣ እንደሚችል እገምታለሁ፡፡ እንደምታስታውሱት ይሄ ጥያቄ "በወያኔ እርሾ አንዲት ኢትዮጵያን ማሰብ አይቻልም! ማስጠንቀቂያ ለአዲሱ ንቅናቄ!" በሚል ርእስ ሰሞኑን "የኢትዮጵያ ሀገራዊ ንቅናቄ" በሚል ሥያሜ የተጣመሩ ድርጅቶችን ከተቃወምኩበት ጽሑፌ ለዛሬ በይደር ያቆየነው ጥያቄም ነው፡፡

ከዓመታት በፊት ጀምሬ በተለያዩ በጻፍኳቸው ጽሑፎቸ ወያኔንና ሌሎች ዘውገኛ ድርጅቶችን በምሳሌነት በማቅረብ የዘውግ ወይም ጎሳ ተኮር ፖለቲካ በምን በምን ምክንያት ኋላ ቀር ኢሰብአዊ ኢዲሞክራሲያዊና ጎጅ እንደሆነ ሳስረዳ መቆየቴ ይታወሳል፡፡ አንኳር አንኳሩን ለማስታወስ ካስፈለገ፦

1. አንድ የፖለቲካ ድርጅት "የእከሌ ብሔረሰብ ነጻአውጪ ድርጅት ነኝ!" ብሎ ጎሳው ላይ አተኩሮ በሚታገልበት ጊዜ ከዘውግ አስተሳሰብ ተፈጥሯዊ ችግር የተነሣ ያ ድርጅት ሰብአዊ የሆነው የአመለካከት አድማሱ ይጠብና አስተሳሰቡ ሙሉ ለሙሉ "መብቱን ነጻነቱን አስጠብቅለታለሁ! መሥዋዕትነትን እከፍልለታለሁ!" ወይም "ከፍየለታለሁ!" በሚለው ጎሳው ዙሪያ ብቻ የታጠረ ያነጣጠረ ይሆንና ለሌሎች ዜጎች ወይም ብሔረሰቦች ያለው አመለካከት አሉታዊ ይሆናል ወይም ታገልኩለት መሥዋዕትነት ከፈልኩለት ከሚለው ጎሳው ጋር እኩል ለማየት እጅግ እንዲቸገር ወይም እኩል መመልከት እንዳይችል ያደርገዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ከባባድ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን፣ የአስተዳደር በደሎችን ከዚያም አልፎ ከዘውገኝነቱ በመነጨ ችግር "የጎሳየ ጠላት! ወይም ተቀናቃኝ ነው!" ብሎ ለመፈረጅ በተገደደው ብሔረሰብ ላይ የዘር ማጥራትና ማጥፋት ወንጀሎችን እስከመፈጸም ድረስ እንዲገደድ ያደርጋል፡፡

2. በሀገሪቱ ያሉ ጎሳዎችና ብሔረሰቦች አስተሳሰባቸውና አመለካከታቸው በዘውገኛ ፖለቲከኞቻቸው ጠባብ የአስተሳሰብ አድማስ ልክ ስለሚቀነበብ አስተሳሰብ ፍላጎት ትኩረታቸው ሁሉ ጎጥ ላይ ብቻ የተወሰነ የተገደበ የታጠረ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ በዚህ ችግር ምክንያትም የሀገር ፍቅር ከትውልዱ ወይም ከሕዝቡ ይጠፋል፣ አንዱ ጎሳ ወይም ብሔረሰብ ሌላውን እንደ ባዕድ እንዲመለከተውና "የኔ" ከሚለው ጎጡ በግዳጅ ወይም በኃይል እስከማስወጣት ወይም ማባረር ድረስ ዳርጎ በአንድ ሀገር ሕዝብ መሀል አንድነት ፍቅር መተሳሰብ እንዲጠፋና ሀገርን ባለቤት ተቆርቋሪ እንድታጣ በመጨረሻም ሀገርንና ሕዝብን እጅግ ለተወሳሰበ ችግር ዳርጎ ሀገሪቱ ተገነጣጥላ እንድትፈርስ ያደርግና በፈረሰችው ሀገር የሚኖረውን ሕዝብ ኑሮ ወይም ሕይዎት ሲኦል እንዲሆን ያደርጋል፡፡

3. ከላይ እንዳልኩት በሥልጣን ላይ ያለው አገዛዝ የዘውግ ፖለቲካን አቀንቃኝ በሚሆንበት ጊዜ ከዘውገኝነት ተፈጥሯዊ ችግር በመነጨ ለራሱ ጎሳ ማድላቱ መሥዋዕትነትን ከፍየለታለሁ የሚለውን ጎሳውን በተለየ ሁኔታ ለመጥቀም ጥረት ማድረጉ አይቀርምና ከራሱ ጎሳ ውጪ ባለው ሕዝብ ዘንድ ያለመታመን ችግር ይገጥመዋል፣ ከራሱ ጎሳ ጎጥ ውጪ ለሀገሪቱ አዋጪ የሆነ ታላላቅ የልማት ሥራዎች በመንግሥት መሠራት በሚኖሩበት ጊዜ ዘውገኛው አገዛዝ ተመቅኝቶ የልማት ሥራው እንዳይታሰብ ያደርጋል፣ በአጋጣሚ ሕዝቡ

ወይም የሆነ አካል አገዛዙን ሲያሳስብም የተለያየ ምክንያትና መሠናክል በመፍጠር ተግባራዊ እንዳይሆን ያደርጋል፣ ያለ አዋጭነቱ ያለ ተስማሚነቱ ያን ሥራ የጎሳው በሆነ ቦታ ላይ እንዲሠራ ያደርጋል ወይም ይሄንን ሥራ በሌላ ተስማሚ ሥራ ለውጦ የጎሳየ በሚለው ቦታ እንዲሠራ በማድረግ አድልኦ በመፈጸም ሀገር እንዲያከስር ሕዝብ እንዲበድል ያደርጋል፡፡ ይህ በሀገሪቱ ምቹ አዋጪ ወይም ተስማሚ በሆነ ቦታ በመንግሥት መሠራት ያለበት ታላቅ ለሀገሪቱ አዋጭና ጠቃሚ የሆነው የልማት ሥራ በአንገብጋቢነቱ ምክንያት የግድ መሠራት ኖሮበት ዘውገኛው አገዛዝ የግዱን እንዲሠራው ተደርጎ የሚሠራ ከሆነም በዜጎች ወይም በሌሎቹ የሀገሪቱ ጎሳ ወይም ብሔረሰቦች ዘንድ በሰፈነው ጎሳ ተኮር አስተሳሰብ ምክንያት ያን የሀገር የልማት ሥራ የነሱም መሆኑን እንዳይረዱ ስለሚያደርጋቸው ልማቱ ለሀገሪቱ ያለው አዋጭነትና ጠቃሚነት ሳይሆን የሚታየውና የሚታሰበው የዚያ ቦታ ባለቤት ጎሳ በተለየ ተጠቃሚ የሚሆን እንደሆነ ታስቦ የሀገሪቱን የማድረግ አቅም ባለማገናዘብ የዚያን ተመጣጣኝ የሆነ የልማት ሥራን ለየራሳቸው እንዲሠራ እንዲጠይቁ ካልተሠራ በፍትሐዊነት ተጠቃሚ ያልሆኑ እንደሆኑ እንዲያስቡ አድርጎ የሀገር ህልውና አደጋ ላይ እስኪወድቅ ድረስ ያለመረጋጋትና የቀውስ መንስኤ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

4. ኢትዮጵያ ውስጥ ከ 80 በላይ ብሔረሰብና ጎሳ ያለ ቢሆንም ወደ ዜጎች ማንነት ስንወርድ ግን እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ስለ ትክክለኛ ማንነቱ ወደ ኋላ ያለውን ትውልዱን መረጃ አግኝቶ ትክክለኛ ማንነቱን የማወቅ ውስንነት ካልገታው በስተቀር ከሦስትና ከአራት ብሔረሰብ ወይም ጎሳ ያልተወለደ አንድም ዜጋ ፈጽሞ የሌለ ሆኖ ሳለ በረጅሙ የሀገራችን ሕዝብ የአንድነት ታሪክ ሒደት ተፈጥሯዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ መስተጋብር እንዲህ ተቀይጦ ተዋሕዶ አንድ የሆነን ሕዝብ ከፋፍሎ ዝምድናውን፣ የደም ትስስሩን፣ አንድነቱን አፍርሶ መለያየትን ግጭትን ሌሎች አደገኛ ቀውሶችንም አምጥቶ ሕዝብን ለመከራ ለሰቆቃ የሚዳርግ በመሆኑ፡፡ በሩዋንዳ አሁን ባለው አሥተዳደር "እኔ ቱትሲ ነኝ! ፣ እኔ ሁቱ ነኝ!" ብሎ ራስን በብሔረሰቡ ወይም በጎሳው ማንነት መግለጥ ወንጀል ወይም ክልክል የተደረገው ዘውግ ወይም ጎሳ ተኮር አስተሳሰብ አስከፊ ምስቅልቅል ውስጥ ከቶ ከፍተኛ ዋጋ ስላስከፈላቸው ነው፡፡ የዘር ልዩነትን ምክንያት ያደረገ የእርስ በእርስ ፍጅት እጅግ አሰቃቂ የመከራ ዘመን ያሳለፈችው ሀገር ሩዋንዳ ዜጎች ዛሬ "እኔ ሩዋንዳዊ ነኝ!" ይላሉ እንጅ የፈለገ ቢሆን "እኔ ቱትሲ ወይም ሁቱ ነኝ!" አይሉም፡፡ "ብልጥ ከሌላው ይማራል!" እኛ የዘውግ ወይም የጎሳ አስተሳሰብ እጅግ ጎጂ እንጅ ፍጹም ጠቃሚ አለመሆኑንና ተዋልደን ተዋሕደን አንድ እንደመሆናችን መጠን "እኔ ኢትዮጵያዊ ነኝ!" ብለን እራሳችንን ከመግለጥ ይልቅ ጎሳችንን ወይም ብሔረሰባችንን እየጠራን ራሳችንን መግለጥ ስሕተት መሆኑን ለመረዳት የግድ ሩዋንዳውያን ባለፉበት የእሳት መንገድ ውስጥ ማለፍ አለብን ወይ???

5. በአንድ ሀገር ውስጥ አገዛዙ ዘውገኛ በሚሆንበት ጊዜ የራሱን ጎሳ ጥቅም ለማስጠበቅ ሲል ሌሎች ጎሳዎችን እርስ በእርስ ለማጋጨት በሚያደርገው ሸፍጥ የተሞላበት ሴራ ሰላምና መረጋጋት ከዚያች ሀገር እንዲጠፉ ያደርጋል፡፡ በምሳሌ ለማስረዳት ያህል እንደምታስታውሱት የደርግ ውድቀት አቅራቢያ ላይ ወያኔና ሸአቢያ ኦነግን በመጠቀም ወለጋ ላይ አንድ የፈጸሙት ዘግናኝ ግፍ አለ፡፡ ያ ዘመቻ ሦስቱም በጥምረት ያደረጉት ዘመቻ ነበር፡፡ የፈጸሙትን ግፍ የፈጸሙት በጋራ ነው፡፡ እንዲናፈስ ያደረጉት ግን ኦነግ ብቻውን እንደፈጸመው አድርገው ነው፡፡ የዚህ ምክንያትም ከኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዙት አማራ እና ኦሮሞ በመሆናቸው ወያኔ እና ሸአቢያ "ሥልጣን መያዝ ካለብን እነኝህን ሁለት አብላጫ ቁጥር ያላቸውን ብሔረሰቦች የግድ ማጋጨት ማናከስ ዘለዓለማዊ ቁርሾ ውስጥ መክተት ይኖርብናል!" ብለው በማመናቸው በዚያ ዘመቻ ላይ ወለጋ በአብዛኛው በተባበሩት መንግሥታት የተራድኦ ድርጅት ጥበቃ ስር የነበሩ አማሮችን ለቅመው ትምህርት ቤት የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ እያጎሩ በከባድ መሣሪያዎች ደብድበው ከፈጇቸው በኋላ አቃጠሏቸው፡፡ ኦነግ ብቻውን እንዳደረገውም አስወሩ፡፡

ደርግ ከወደቀ በኋላም ይሄንን ሴራቸውን ቀጥለውበት በሀገሪቱ የተለያዩ ቦታዎች ኦነግ በአማሮች ላይ

ግፍ እንዲፈጽም በማድረግ አማራንና ኦሮሞን በጠላትነት እንዲፈላለጉ አድርገዋል፡፡ ይሄንን ዘዴ ፋሺስት ጣሊያንም ተጠቅሞበት በ 5 ዓመቱ የወረራ ወቅት በእውነተኛ ታሪኮች ላይ ለበቀል የሚያነሣሡ የፈጠራ ወሬዎችን እየደባለቀ በማውራት በአማሮች ላይ ዛሬ ወያኔ ኦሮሚያ እና ደቡብ ብሎ ከሚጠራው የሀገራችን ክፍሎች ለወሬ የማይመች ዘግናኝ መጠነ ሰፊ ጥቃቶች እንዲፈጸም ማድረጉ ይታወሳል፡፡ ዛሬም ወያኔና ሸአቢያ ለተመሳሳይ ዕኩይ ሰይጣናዊ ዓላማ የፋሺስት ጣሊያንን የፈጠራ ወሬዎች እያራገቡ ጭምር ዓላማቸው ግቡን እንዲመታ ማድረግ ችለዋል፡፡ አነግ መጠቀሚያ እንደሆነና ወያኔና ሸአቢያ ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ አጃጅለውት ለራሱና እወክለዋለሁ ለሚለው የኦሮሞ ሕዝብ ባጠቃላይ ለሀገሪቱ የማይጠቅም የሞት ወጥመድ ውስጥ እንደከተቱት እስከዛሬ ድረስ ሊረዳ አለመቻሉ እጅግ የሚገርመኝ ጉዳይ ነው፡፡

6. ለመዋዕለ ንዋይ ፍሰት (ለኢንቨስትመንት) ፀር ስለሆነ፡፡ እንደምታውቁት መዋዕለ ንዋይ አፍሳሾች ገንዘባቸውን በአንድ ሀገር ላይ ለማፍሰስ የሚያፈሱበት ሀገር ፍጹም ሰላማዊና የተረጋጋ ሀገር እንዲሆን ይጠብቃሉ፡፡ ከዘውገኝነት በመነጨ ችግር እንደኛ ሀገር ሕገ ወጥና ግብር ቀረጥ የማይከፍሉ እንደ ኤፈርት ያሉ የጎሳና የቡድን የንግድና የመዋዕለ ንዋይ ድርጅቶች እንደፈለጉ በሚሆኑበትና በሌሎች ከዘውግ አስተሳሰብ በሚመነጩ ችግሮች በሚታመስ ሀገር ካላበዱ በስተቀር እግራቸውን አያነሡም፡፡ ወያኔ መዋዕለ ንዋይ አፍሳሾችን ለመሳብ "ሰባ በመቶ አጠቃላይ ወጪቹህን እኔ እችላቹሀለሁ" እያለ ብዙ ጥረት ቢያደርግም አጭበርብረው የሀገር ገንዘብ በልተው ከጠፉና ውጤታማ ካልሆኑ ከጥቂት ከቻይና ከሕንድና ከአንዳንድ ከሌሎችም አጭበርባሪ ድርጅቶች በስተቀር ሀገሪቱ ያላትን እምቅ አቅም ያህል ማንንም ሊስብና ሊታመን ያልቻለው በዚህ ችግር ምክንያት ነው፡፡

እነኝህ የተጠቀሱት ብቻ አይደሉም የዘውግ ፖለቲካ ጠንቀኛ ውጤቱና ኪሳራው በርካታ ነው፡፡ ይሄንንም የዘውግ ፖለቲካ የሚያመጣውን ቀውስ ተገነጣጥሎ ከመፈራረስ በመለስ ያለውን ሁሉ በዚህ 25 ዓመታት የወያኔ አገዛዝ በሀገራችን ዓይተን አረጋግጠናል፡፡ የመገነጣጠሉ ነገርም "የዚህ የዚያ ጎሳ ነጻ አውጪ!" የሚሉ ዘውገኛ ድርጅቶች በግልፅ ዓላማቸው ይሄ እንደሆነ ግልጽ አድርገዋልና ግልጽ የሆነ ሥጋት እስካለ ጊዜ ድረስ በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያን እንዳለች ወይም እንደምትኖር ልንቆጥር አንችልም፡፡ የዘውግ ፖለቲካ በሠለጠነው ዓለም የተጠላ የተናቀ የተወገዘበት ምክንያትም ሀገርንና ሕዝብን ለእንደነዚህ ዓይነቶች ቀውስ ምስቅልቅል የሚዳርግ፣ የሥልጣኔ የሰላም የልማት ፀር፣ የዘውገኝነት አስተሳሰቡ "ዜጎች ያለ አድሎና ልዩነት በሰውነታቸውና በችሎታቸው ብቻ መመዘን መወዳደር አለባቸው!" ከሚለው ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ የበሰለ የሠለጠነ ፍትሐዊና ትክክለኛ አስተሳሰብ ሰዎችን አውጥቶ ዘርን ማዕከል በማድረግ በተፈጥሮው ልዩነትንና አድልኦን ወደሚያስተናግደው ኢዲሞክራሲያዊ ጠባብና ያልበሰለ ያልሠለጠነ የደነቆረ ጎጂ አስተሳሰብ ውስጥ ስለሚከት ስለሆነ ነው በሠለጠነው በምዕራቡ የዓለማችን ክፍል የተጠላው የተወገዘው የተከለከለው...

እያልኩ ነበር ለዓመታት በጽሑፎቸ ሳስተምር ስመክር ስገስጽ የኖርኩት፡፡ በእርግጥ ከዘውገኞቻችን ጥቂት የማይባሉ የተለወጡ ቢሆንም እንዳለመታደል ሆኖ የሚበዙት ግን የሚማሩ የሚለወጡ የሚሠለጥኑ ሆነው ተለውጠው ሠልጥነው ተስተካክለው የሀገራችን ፖለቲካ ሊስተካከል ባይችልም ቅሉ፡፡

ታዲያ የዘውግ ፖለቲካ እንዲህ ዓይነት ችግር ካለው እንዴት "የአማራ" ብለህ አንተም ዘውግን መሠረት ያደረገ የፖለቲካ ድርጅት መመሥረት አለበት! ዘውገኝነትንም ያጠፋል ትላለህ? የሚለውን ጥያቄ ወደመመለስ ስንሻገር፦

በቅድሚያ ይህ የአማራ የፖለቲካ ድርጅት የሚመሠረትበት ዓላማ እንደሌሎቹ ሀገር ማቋቋም ማለት የራሱን በቂና ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት (ሪሶርስ) እና ሌሎች ተመሳሳይ መሠረታዊና ወሳኝ ጉዳዮችንና ሁኔታዎችን የግድ የሚጠይቅ ጉዳይ መሆኑን ሳያውቁ፣ ከመጻኢና ነባራዊ ዓለማቀፋዊ ሁኔታዎች አንጻር ፍጹም አዋጪ አለመሆኑን ሳይረዱ ሀገር መመሥረት ማለት ማሳ ማበጀት መስሎ እንደሚሰማቸው በተጨባጭ ግን

የትኛቸውም ቢሆኑ ከኢትዮጵያ ቢገነጠሉ እንደ ሀገር የመቆም አቅምና ምቹ ሁኔታ እንደሌላቸው ፍጹም እንደማያውቁትና መረዳት እንደማይችሉት የታወሩ ዘውገኛ ድርጅቶች በዚህ የደነቆረ የጎጥ አስተሳሰብ ታንቆ የመገንጠልን ዓላማ አንግቦ የሚንቀሳቀስ ዕውርና ደንቆሮ ዘውገኛ ድርጅች ሳይሆን መግቢያየ ላይ እንደገለጽኩት የሀገራችንን ፖለቲካ ከዚህ ከኋላ ቀሩ የዘውግ አስተሳሰብ አውጥቶ እንደ ምዕራባውያን ሀገራት የሠለጠነና ከዘውግ ነፃ የሆነ የፖለቲካ ምኅዳር በመፍጠር ፍጹም መስፍነ ሕዝባዊት (ዲሞክራሲያዊት) ኢትዮጵያን እውን ማድረግን ዓላማ አድርጎ የሚንቀሳቀስ በመሆኑ ከላይ የዘረዘርኳቸው የዘውግ ችግሮች የሚያሰጉት አይሆንም፡፡ በዚህም ላይ ድርጅቱ የሚያቅፈው አማራንና በከፊል የአማራ ደም ያለባቸውን ብቻ ሳይሆን ከንቃተ ሕሊናቸው ማደግ፣ ከመማር መሠልጠናቸው፣ ከማስተዋላቸው የተነሣ ኋላቀሩንና ያልሠለጠነውን ጎጅነቱ ተነግሮ የማያበቃለትን የዘውግ አስተሳሰብ ንቀውና ጠልተው ዜጎችን በሰውነታቸው ብቻ እኩል በመመልከት ሀገር አቀፍ፣ የአንድነትና የእኩልነት አስተሳሰብን የያዙ የሚያቀነቅኑትን ሁሉንም ኢትዮጵያውያን በመሆኑ ከዘውገኝነት ተፈጥሯዊ ባሕርይ የሚመነጩ ችግሮች በሙሉ ይሄንን ድርጅት የሚያሰጉት አይሆንም፡፡

ድርጅቱ በአማራ ስም የሚመሠረትበት ምክንያቶች፡-

1 ኛ. እንደምታዉቁት በሀገራችን በኢትዮጵያ አንድ ዘልማዳዊ አስተሳሰብ አለ፡፡ ሁሉም ብሔረሰብ በዘውግ አስተሳሰብ ታጥሮ ጎጥ ጎጡን ሲያስብ ኢትዮጵያን የአማራ አድርጎ የማሰብ፣ አማራ ይጨነቅላት የማለት፣ አንድ ሰው የኢትዮጵያ ነገር ከከነከነው "አማራ ነህ እንዴ?" ፣ የአንድነት አስተሳሰብ ካንጸባረቀ አሁንም "አማራ ነህ እንዴ?" ፣ የታሪክ የማንነት የቅርስ ጉዳይ ካሳሰበው "አማራ ነህ እንዴ?" ይባላል፡፡ ባጠቃላይ የኢትዮጵያ ጉዳይ ለአማራ የተተወ ነው፡፡ ይሄ ከሆነና ከታመነበት ዘንዳ አማራ ኃላፊነቱን በይፋ ተቀብሎ የቀደመ ልምዱን፣ ብቃቱን፣ ችሎታውን፣ ተቆርቋሪነቱን፣ አሳቢነቱን፣ የኃላፊነት ስሜቱን፣ ባለአደራነቱን ወዘተረፈ. ተጠቅሞ ይሄንን ችግር የመቅረፍን ጉዳይ ቢሠራበት ውጤት ሊገኝ ይችላል ከሚል ቀና አስተሳሰብ ሲሆን፡፡

2 ኛ. ያሉት የአንድነት ወይም ሀገር አቀፍ የፖለቲካ ድርጅቶች በወያኔና አጋሮቹ ለዘመናት በአማራ ሕዝብ ላይ እየተፈጸመ ያለውን ሰፊና እጅግ አደገኛ የዘር ማጥፋትና ማጽዳት በሰው ልጆች ላይ የሚፈጸም የመጨረሻ ወንጀል በግልጽ በይፋ እያወገዙትና የሚገባውን ትኩረት ሰጥተው እየታገሉት ባለመሆኑ የዚህች ሀገር ባለውለታ ሕዝብ የአማራ ህልውና እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ በመድረሱ ለዚህ ሰይጣናዊ የጥፋት ተልዕኮ በቂ ትኩረት ሰጥቶ አደጋውን የሚቀለብስ ኃይል በማስፈለጉ፡፡

3 ኛ. ያሉት የአንድነት ወይም የሀገርአቀፍ የፖለቲካ ድርጅቶች ጎጅውንና ኋላቀሩን የዘውግ ፖለቲካን የምንቃወም የምናወግዝ ነን እያሉ መልሰው ደግሞ ከእነኚህ የዘውግ ድርጅቶች ጋር ጥምረት ትብብር ቅንጅት ግንባር እየፈጠሩ በዚህች ሀገር ዘውገኝነት ጎጂ መሆኑ ታውቆ ሊከስም የሚችልበትን ዘመን እያራዘሙትና ለመርሖዋቸውና ለርዕዮተዓለማቸው ታማኝና ጽኑ ሆነው ባለመገኘታቸው፡፡

ይሄንን ስል "ከዘውግ ድርጅቶች ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት መፈጠር የለበትም!" አይደለም እያልኩ ያለሁት፡፡ ዘውገኞቹን ግንዛቤያቸው እንዲያድግ አስተሳሰባቸው እንዲበስልና ከዘውገኝነት እንዲወጡ መሠራት ይኖርበታል፡፡ ነገር ግን ዘውገኞቹ ዘውገኝነት የማይጠቅምና ጎጂ መሆኑን ተረድተው ከሥያሜያቸው ጀምሮ ይሄንን አስተሳሰብ ሳይተውና ውጤቱ ውሕደት ሆኖ በአዲስ ሥያሜ ሊወጣ የማይቻልበትን ድርድርንም ሆነ ውይይትን አድርጎ ጥምረትን፣ ንቅናቄን፣ ቅንጅትን፣ ግንባርን ከዘውግ ድርጅቶች ጋር መፍጠር ፍጹም ስሕተትና ዘውገኝነትንም ማበረታታትና መደገፍ በመሆኑ የጥምረትን የግንባርን የቅንጅትን የትብብርንም ሆነ የንቅናቄን ግንኙነቶችን ከዘውግ ድርጅቶች ጋር ማድረግ ፍጹም ተገቢ አይደለም፡፡

4 ኛ. ሰፍኖ ባለው ጠባብ የዘውግ ወይም ጎሳ ተኮር ፖለቲካ ምክንያት ዘውገኞቹ ወያኔና አጋሮቹ ለአማራ ባላቸው ፍጹም አግባብ ያልሆነ ጥላቻ የአማራን አሻራ ከሀገራችን ታሪክና ሥልጣኔ ለማጥፋት ሲሉ

በሚሠሩት ፍጹም ኃላፊነት የጎደለው የጥፋት ተግባር የአማራ ትሩፋትና የሀገር ሀብት ማንነት ታሪክ ደብዛው እንዲጠፋ እየተደረገና ሀገሪቱ ታሪክ ማንነት ቅርስ ሥልጣኔ አልባ እየሆነች በመሆኑ ይህ ሰይጣናዊ ዘመቻ ያጠፋቸውን እሴቶች ጠፍተው ሳይቀሩ የሀገርና የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀብት ናቸውና፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ የቀጥታም ይሁን የተዘዋዋሪ አስተዋጽኦ አለባቸውና ነፍስ እንዲዘሩ የማድረግ ሥራ መሠራቱ አስፈላጊ በመሆኑና በመሳሰሉት ምክንያቶች ነው፡፡

*ሥያሜ፡-*

የዚህ የፖለቲካ ድርጅት ስም "ጃንቶሐራ" እንዲባል ሐሳብ አቀርባለሁ፡፡ ቃሉ ከአማራና ከኢትዮጵያ ማንነት ታሪክ ጋር የተሳሰረ ቅድመ ታሪክ የነበሩ የጥንታዊ ቃላት ጥምረት ነው፡፡ ጃን ማለት ታላቅ ማለት ነው፡፡ ጃንሆይ (ታላቅ ወይም ንጉሥ ሆይ!) ጃን ሜዳ (ታላቅ ሜዳ)፣ ጃን ተከል (ታላቅ ሰው ወይም ንጉሥ የተከሉት) እንዲሉ፡፡ ቶ ደግሞ የእግዚአብሔር ስም ነው፡፡ የአማሮች ወላጆች እንደሆኑ የሚነገርላቸው የመጀመሪያዎቹ አፍሪካውያን የግብጽ በኋላም የኢትዮጵያ መሥራችና አቅኚ ጥቁር ኩሻዊ ሕዝብ በጥንት ዘመን ይህችን ምድር ኢትዮጵያን ቶ ኔቶር (የእግዚአብሔር ሀገር) ሲሉ ይጠሯት ነበር፡፡

ዛሬ አማሮች ሴማዊ ማንነት ሊኖራቸው የቻለው በአንዳንዶቹ ሳባውያን በመባል የሚጠሩት ውሑዳን ከደቡብ ዓረብ ተሻግረው ስለተዋሐዷቸው ነው፡፡ ሐራ ማለት ሕዝብ ማለት ነው፡፡ አምሐራ (አም ነጻ ሐራ ሕዝብ፤ ነጻ የሆነ ወይም ነጻነት ያለው ሕዝብ) እንደመሆኑ፡፡ ባጠቃላይ ጃንቶሐራ የሚለው ቃል "ታላቅ የእግዚአብሔር ሕዝብ!" የሚል ማንነቱን ታሪኩን የሚገልጽ ትርጉም የያዘ ጥንታዊ ቃል ነው፡፡ በመሆኑም ኢትዮጵያን ከጎጂና ኋላ ቀር የዘውግ ፖለቲካ አውጥቶ እንደምዕራባውያን ሁሉ ከአድልኦ ነጻ የሆነ ሰብአዊነትን ብቻ ማዕከሉ ያደረገ ከዘውግ ነጻ የሆነ የሠለጠነና ትክክለኛ ፖለቲካ ለማሸጋገር፣ የዘውግ ፖለቲካ የፈጠራቸውን ሌሎች ችግሮችን አስወግዶ ሁሉም ዜጋ በዕኩልነት የሚስተናገድባት፣ ሕዝብ የሥልጣን ባለቤት የሚሆንባት፣ በመረጠው ይሁንታ በሰጠው አካል ብቻ የሚተዳደርባት ሀገር አድርጎ ኢትዮጵያን ፍጹም መስፍነ ሕዝባዊት (ዲሞክራሲያዊት) ለማድረግ የሚቋቋመው የፖለቲካ ድርጅት "ጃንቶሐራ" ይባላል ማለት ነው፡፡ ይህ ድርጅት ይሄንን ግቡን እንዳሳካ ህልውናው የሚያከትም ይሆናል፡፡

ማን ያቋቁመዋል? እንዴት? ለሚለው የሚቋቋመውን ድርጅት ከጠለፋ ለመጠበቅ ሲባል የመመሥረቱን የቤት ሥራ እስከአሁን ማንነታቸው በሕዝብ ዘንድ በሚገባ ለሚታወቁ እንደ ፀረ ወያኔ የአንድነት ኃይሎች ብንሰጠው መልካም ይመስለኛል፡፡ እንዲያው አንድ ጠቁመን ካላቹህኝ ሞረሽ ወገኔን እጠቁማለሁ፡፡ ሞረሾች ከመሰሎቻቸው ጋር በመሆን በአጭር ጊዜ ውስጥ ይሄንን ድርጅት በተሳካ ሁኔታ እንዲመሠረትና ወደትግሉ ሜዳ እንዲገባ እንደሚያደርጉት ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ጃንቶሐራ የት ሆኖ ይታገላል? ካላቹህኝ አሁን ባለው ሁኔታ ይህ ጉዳይ የሚያሳስብ አይደለም፡፡ እዚሁ ሀገራችን ውስጥ ሕዝባችን የደረሰበትን መነቃቃት በመጠቀም በግልጽና በኅቡዕ ታግሎ ለድል ይበቃል!!! ሁሉንም ዓይነት የትግል ስልት ይጠቀማል፡፡

ይሄ ማለት ግን ችግሮችን በድርድር ለመፍታት በሚል ከወያኔ ጋር ለመደራደር ይቀመጣል ማለት አይደለም፡፡ ወያኔ ያሳጣንን የሀገራችንን ብሔራዊ ጥቅሞች ለማስጠበቅ ሲባል ወያኔ በሕዝብ ሳይመረጥ ሕዝባዊ ይሁንታን ሳያገኝ በኃይል ሥልጣንን እንደጨበጠ የግድ በኃይል መወገድ ይኖርበታልና በምንም ተአምር ቢሆን ጃንቶሐራ ከወያኔ ጋር ለድርድር አይቀመጥም! ለወያኔ መንግሥትነትም ዕውቅና አይሰጥም!

በመጨረሻም እከሌ ከእከሌ ሳይባል ምሁር ጎጋ፣ ወንድ ሴት፣ ወጣት ሽማግሌ፣ ገጠሬ ከተሜ፣ ተማሪ ሠራተኛ ወዘተረፈ. ሳይባል፤ አሁን ላይ በሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ ሆናቹህ እየታገላቹህ ያላቹህትን ሁሉ ጨምሮ ይሄንን የተቀደሰ ዓላማ የምትጋሩ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ጃንቶሐራን ትቀላቀሉ ዘንድ በታላቅ አክብሮት ተጋብዛቹሀል፡፡

ሁሉም ለወሳኙ ትግል ራሱን ያዘጋጅ!!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ /ኪዳን አርጋው
amsalugkidan@gmail.com

http://www.ethiopanorama.com